www.fag.gov.et

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ — ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No. 6
ADDIS ABABA - 24th August, 1995

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮/፲፱፻፹፯ ዓ·ም·
የደህንነት ፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ..... ገጽ ፷

CONTENTS

Proclamation No. 6/1995
Security, Immigration and Refugee Affairs Authority Establishment Proclamation ..... Page 60.

አዋጅ ቁጥር ፮/፲፱፻፹፯

የደህንነት ፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የደህንነት ፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞችን ጉዳይ ባለሥልጣን ማቋቋም በማስፈለጉ ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የደህንነት ፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፮/፲፱፻፹፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪. መቋቋም

፩. የደህንነት ፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" ተብሎ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል ።

፫. የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ማቋቋም ይችላል ።

PROCLAMATION NO. 6/1995

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE SECURITY, IMMIGRATION AND REFUGEE AFFAIRS AUTHORITY

WHEREAS, it has become necessary to establish the Security, Immigration and Refugee Affairs Authority;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Security, Immigration and Refugee Affairs Authority Establishment Proclamation No. 6/1995."

2. *Establishment*

1. The Security, Immigration and Refugee Affairs Authority (hereinafter referred to as the "Authority") is hereby established as an autonomous public institution of the Federal Gogvernment.

2. The Authority shall be accountable to the Prime Minister.

3. *Head Office*

The head office of the Authority shall be in Addis Ababa and it may establish branch offices elsewhere as may be necessary.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 1·60

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹፻፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

www.fag.gov.et

፬. የባለሥልጣኑ ዓላማ

የባለሥልጣኑ ዓላማ የሃገሪቱንና የሕዝብ ደህንነት ፣ የኢሚግሬሽን ፣ የዜግነትና የስደተኞች ፖሊሲዎችና ሕጐችን ማስፈጸም ይሆናል ።

፭. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፣

፩. የአገርንና የሕዝብን ደህንነት ጥበቃ ፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ፖሊሲዎች ያዘጋጃል ፣ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል ፤

፪. በሃገር ውስጥና በውጭ አገር የአገርንና የሕዝብን ደህንነት ጥበቃ ሥራ በኃላፊነት ይሠራል ፤

፫. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ ነፃነትና ኢኮኖሚ ላይ የሚጠነሰሰውን ማናቸውንም ሴራ ይከታተላል፣ ያጣራል ፣ እንደ ሁኔታው አግባብ ላለው ክፍል ያሳውቃል ፤

፬. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጭ ሃገር ዜጐች እንዲመዘገቡ ያደርጋል ፣ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡና ከአገር እንዲወጡ እንዲሁም በአገር ውስጥ እንዲዘዋወሩ ፈቃድ ይሰጣል ፤

፭. አግባብ ካላቸው የመስተዳድር አካላት ጋር በመተባበር ጥገኝነትና የኢትዮጵያ ዜግነት እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ሰዎችን ጉዳይ እያጣራ ውሣኔ እንዲያገኙ ያደርጋል ፤

፮. ከዲፕሎማቲክ ፓስፖርት በስተቀር ለዜጐች ፓስፖርት ይሰጣል ፣ እንዲሁም ለማንኛውም ሰው የመጓጓዣ ሰነድ (ቪዛ) ይሰጣል ፤

፯. አግባብ ካላቸው አካላትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ስለስደተኞች ጉዳይ ኃላፊ ይሆናል ፤

፰. የጦር መሣሪያ ፣ የተኩስ መሣሪያ ወይም ፈንጂ ለመያዝ ወይም በእነዚሁ ለመጠቀም ፈቃድ ይሰጣል ፣ ፈንጂ ስለሚሸጥበት ሁኔታ ይወስናል ፣ ፈንጂ ለሚሸጡና የጦር ወይም የተኩስ መሣሪያ ለሚያድሱ ፈቃድ ይሰጣል ።

፮. የባለሥልጣኑ አቋም

ባለሥልጣኑ ፡

፩. በመንግሥት የሚሾም አንድ ኃላፊ ፤ እና

፪. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፯. የኃላፊው ሥልጣንና ተግባር

፩. ኃላፊው የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል ፣ ያስተዳድራል ።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኃላፊው ፤

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፭) የተመለከተውን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል ፤

ለ) በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል ፤

4. Objective

The objective of the Authority shall be to execute policies and laws on state and public security, immigration nationality and refugees.

5. Powers and Duties of the Authority

The Authority shall have the following powers and duties:

1. to formulate policies and strategy concerning state and public security as well as immigration and refugee affairs;
2. to be responsible for internal and external state and public security activities;
3. in cooperation with the appropriate organs, to follow up and investigate any conspiracy against the Ethiopian independence and economy, notify the appropriate organ of same;
4. in cooperation with the appropriate organs, to provide for the registration and issuance of entry and exit permits to foreign nationals as well as premits to move within the Country;
5. in cooperation with the appropriate organs, to investigate and cause decisions to be taken on the cases of persons who apply for asylum and Ethiopian nationality;
6. to issue passports to nationals other than diplomatic passports; issue travel documents (visas) to any person;
7. in cooperation with the appropriate organs and international organizations, to be responsible for matters relating to refugees;
8. to issue licences for the possession or use of arms, firearms and explosives; prescribe conditions under which explosives may be sold; issue permits to persons who deal with explosives and to persons who repair arms and firearms.

6. Organization of the Authority

The Authority shall have:

1. a Head appointed by the Government; and
2. the necessary staff.

7. Powers and Duties of the Head

1. The Head shall be the chief executive of the Authority and, as such, shall direct and administer the activities of the Authority.
2. Without limiting the generality stated in sub-Article (1) of this Article, the Head shall:
   a) exercise the powers and duties of the Authority specified in Article 5 of this Proclamation;
   b) employ and administer employees of the Authority in accordance with the Federal civil service laws;

www.fag.gov.et

ሐ) የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል ፤

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል ፤

ሠ) ባለሥልጣኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙ ነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል ፤

ረ) ስለ ባለሥልጣኑ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል ።

፫. ኃላፊው ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል ።

፮. ውክልና

ባለሥልጣኑ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ሥልጣኑን ለፌዴራል ወይም ለክልል አስፈጻሚ አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል ።

፱. በ ጀ ት

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል ።

፲. የሂሣብ መዛግብት

፩. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪. የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው አዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው አዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ ።

፲፩. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ወይም በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ማናቸውም ሕጐች ወይም መመሪያዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ።

፲፪. መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፭) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ የቀድሞው የሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መብ ና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል ።

፲፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

c) prepare the annual work programme and budget of the Authority and implement same upon approval;

d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work programme of the Authority;

e) represent the Authority in all its dealings with third parties;

f) submit reports on the activities of the Authority.

3. The Head may delegate part of his powers and duties to the other officials and to employees of the Authority to the extent necessary for the efficiency of the Authority.

8. *Delegation*

The Authority may, where it finds it necessary for the performance of its activities, delegate its powers to federal or regional executive organs

9. *Budget*

The budget of the Authority shall be allocated by the Government.

10. *Books of Accounts*

1. The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.
2. The Commission's books of accounts and financial documents shall be audited annually by the Auditor General or by Auditors designated by him.

11. *Inapplicable Laws*

Any laws or directives that contravene this Proclamation or relate to matters provided for herein shall be inapplicable.

12. *Transfer of Rights and Obligations*

The rights and obligations of the former Ministry of Internal Affairs, related to matters specified under Article 5 of this Proclamation, are hereby transferred to the Authority.

13. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 24th day of August, 1995.

Done at Addis Ababa, this 24th day of August, 1995.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE